የሰ/መ/ቁ. 71126
ሰኔ 5 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ወርቅነሽ ሰብስቤ - ወኪል ፍቅርተ እንደሻው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሻለቃ ባሻ እንደሻው - ቀረበ

2. አቶ እሸቱ እንዳሌ - ቀረበ

መዝገቡ ያደረው ለውሳኔ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ክርክር ሆኖ የፍቺ ውጤትን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ሂደት በተሸጠው የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ አመልካች የቀደምትነት መብት ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝቦች ብሔ/ክል/መንግስት በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው ይሄው የክልሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 28-10-2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ባልና ሚስት በሚሸጠው የጋራ ቤት ሽያጭ ሂደት ላይ ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ የፈቀደላቸው ስለመሆኑ፣ በጨረታው ሂደት ግን የአሁን 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ፣ ቀደም ሲልም አመልካች ያመለከቱት የቅድሚያ መብት ጥያቄ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ግን በጨረታው ሂደት ተጫራች ሆነው እንዲሳተፉ መብት የሰጠ እንጅ የቀደምትነት መብት ባለመሆኑ፣ በዚሁ ቀን ጠዋት የተሰጠው ትዕዛዝ ይሄንን ሳያገናዝብ በስህተት ስለመሆኑ በማመላከት የቀረበውን የቀደምትነት መብት ጥያቄን ውድቅ በማድረግ በጨረታው ሂደት ተሳትፎ አሸናፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛ ስለመሆኑ የቀረበውን ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራቀኙን ክርክር በመስማት ይሄንኑ የክልሉ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን ቅሬታ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አሁን የቀረበው አቤቱታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን አመልካች ባቀረበችው የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ያለቻቸውን ነጥቦች በማንሳት የተከራከረች ሲሆን ፍሬ ሃሳቡ፡- ቀደም ሲል የክልሉ የወረዳ ፍ/ቤት ቤቱን ቅድሚያ እንድወስድ የሰጠውን አስገዳጅ ትዕዛዝ በመለወጥ ሌላ ትዕዛዝ መስጠቱ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ባለመሆኑ፣ ስለጋራ ባለሀብትነት ከሚመለከቱት የፍትሐብሔር ድንጋጌዎች አኳያ በቀደምትነት በግዥ ስለማስቀረት መብት ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች አንጻር በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት የሌለው በመሆኑ እንዲታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ታዞ በየራሳቸው ጥቅምት 8 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ባልና ሚስት በሚሸጠው ቤት ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የተደረገ እና በሂደቱ እንደማንኛውም ተሳታፊ ተሳትፈው የተሸነፉ

ስለመሆኑ፣ 2ኛ ተጠሪ በሂደቱ አሸናፊ በመሆን ቤቱን የገዛ በመሆኑ እና 1ኛ ተጠሪም ሆነ ለአመልካች የተሰጠው ዕድል በጨረታው ላይ የመሳተፍ እንጂ የተለየ ነገር በሌለበት ሁኔታ አመልካች የምታነሳው ቅሬታ አግባብነት የሌለው ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ቅሬታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥታለች፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም የተነሱትን ክርክሮች፣ ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲባል ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች ያነሳችው የቀደምትነት መብት ውድቅ መደረግ ስለጋራ ባለሀብት ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር በሚል በመሆኑ ከዚሁ ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው ጭብጥ አኳያ ታይቶ እልባት ማግኘት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሠረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች በፍቺ ውጤት አፈጻጸም ወቅት በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነው ቤት በጨረታ እንዲሸጥ ስለመታዘዙ፣ በዚህን ሂደት ውስጥ ሁለቱም ወገኖች የቀደምትነት መብት መጠየቃቸው፣ ሁኖም ግን ፍርድ ቤቱ በጨረታው ሂደት እንዲሳተፉ እድል በመስጠት እና ለሁለቱም ወገኖች የተለየ መብት ሳይሰጥ የጨረታው ሂደት የተከናወነ ስለመሆኑ፣ በዚህም ሂደት ባልና ሚስት ተሳታፊ የነበሩ ቢሆንም ማንኛቸውም ያላሸነፉ እና በጨረታው ተሳታፊ የነበረው 2ኛ ተጠሪ ያሸነፈ ስለመሆኑ ነው፡፡ አመልካችም ብትሆን ቀደም ሲል ጨረታው ከተከናወነ በኋላ በቅድሚያ እንድወስድ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ፍርድ ቤቱ በስህተት ነው በሚል ማስተካከከያ መስጠቱ አግባብነት የለውም ከሚል በስተቀር ከላይ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በተመለከተ የምታነሳው ክርክር የሌለ ከመሆኑም በላይ ከጨረታው መከናወን በፊት የቀደምትነት መብት ከ1ኛ ተጠሪ በተለየ መልኩ ተሰጥቶኛል የሚል ክርክር የላትም፡፡

በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በመያዝ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት ክርክሩ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በቀጥታ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/1996 መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ የክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 103/1/ መሠረት የፍቺ ውጤትን በተመለከተ በዓይነት ለመከፋፈል አዳጋች የሆነን እና ከተጋቢዎቹ እንደኛው ወገን ለሌላኛው ለመተው መስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈሉ የሚደረግ ስለመሆኑ እና በዚሁ ድንጋጌ ስር በአሻሻጡ ሂደት ግራ ቀኙ ያልተስማሙ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ ደግሞ ሁለቱም ባልና ሚስት ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ለሁለቱም የፈቀደው እንደማንኛውም ተጫራች በጨረታው እንዲሳተፉ የሚል እስከሆነ ድረስ እና ተሳትፈውም አሸናፊው 2ኛ ተጠሪ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አመልካች በተለየ ሁኔታ የቀደምነት መብት ይገባኛል በማለት የምታቀርበው ክርክር አግባብነት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም በጨረታው ሂደት ያሸነፈውን 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ይረከብ በማለት ውሣኔ መስጠታቸው በአግባቡ እና በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 439 እና ተከታዮቹ ስር መሠረታዊ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መርህን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነገር አላገኘንም፡፡

ባጠቃለይ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረበችውን የቀደምትነት ግዥ መብት በተመለከተ ውድቅ በማድረግ በጨረታው መሠረት አሸናፊው ወገን /2ኛ ተጠሪ/ ቤቱን እንዲረከብ በማለት ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡና የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የደቡብ ብሔ/ብሔ/ህዝ ብሔ/ክል/ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝ.ቁ. 54623 በቀን 11/11/2003 ዓ.ም. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝ. ቁ. 10567 በቀን 08/11/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት እና የሀዋሳ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝ .ቁ.21347 በቀን 28/10/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የቀደምትነት ግዥ መብት ወድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ለደረሰው ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ